# ምክር ቤቱ 9ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን አካሄደ

- **የ2010 በጀት ዓመት ሪፖርትና የምክር ቤቱ ሁለት ሰነዶች ፀድቀዋል**



***ከፊት ለፊት፡-*** *ክብርት የኢፌዲሪ ፕሬዚደንት ወ/ሮ ሣህለወርቅ ዘውዴ እና በስተግራ መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር)፣ የም/ቤቱ ፕሬዚደንት*

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት 9ኛውን የምክር ቤቱ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥቅምት 26 ቀን 2011 ዓ.ም. በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል አካሄደ፡፡

የክልልና የከተማ እንዲሁም በተዋረድ ያሉ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የቦርድ አባላትን ጨምሮ 140 በላይ የጠቅላላ ጉባዔው አባላት፣ የቀድሞ የምክር ቤቱ ፕሬዚደንቶች እና የምክር ቤቱ ማኔጅመንትና ሠራተኞች በተገኙበት የምክር ቤቱ የ2010 በጀት ዓመት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በምክር ቤቱ ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) በኩል ተደምጧል፡፡ የበጀት ዓመቱ ኦዲት ሪፖርትም ተነቧል፡፡

በተጨማሪም የምክር ቤቱ የመተዳደሪያ ደንብ እና የምርጫ አፈጻጸም የማሻሻያ አንቀጾች ላይ ገለጻና ማብራሪያ ቀርቧል፡፡

ምክር ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 341/95 በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት የግሉ ዘርፍ በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ ደረጃ በደረጃ ለማሳደግ ንግድና ኢንቨስትመንትን የማስፋፋት፣ የአድቮከሲ እና የአቅም ግንባታ ተግባራትን እንደሚያከናውን የገለጹት የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት ኢንጂነር መልአኩ በበጀት ዓመቱ በሦስቱም ዘርፎች የሚያበረታታ ተግባር ማከናወኑን በሪፖርታቸው ላይ ጠቅሰዋል፡፡

ንግድና ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋት ጋር በተያያዘ በበጀት ዓመቱ በሀገር ውስጥና በሌሎች ሀገራት በድምሩ 20 ያህል የቢዝነስ ፎረሞችና የንግድ ትርዒቶች በውጭ ባለሀብቶችና በሀገር በቀል አቻዎቻቸው መሀል የአቻ ለአቻ የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተው የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች የገበያ ዕድላቸው እንዲሰፋና የዕውቀትና ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ መቻሉ በሪፖርቱ ላይ ተገልጿል፡፡ ሪፖርቱ በማብራሪያው የቢዝነስ ፎረሞቹ የተካሄዱት ከሞሮኮ፣ ህንድ፣ እስራኤል፣ ቱርክ፣ ዮርዳኖስ፣ ጀርመን፣ ደቡብ ኮሪያ፣ አውስትራሊያና ኒውዚላንድ እንዲሁም ሌሎች ሀገሮች ከተውጣጡና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ጨምሮ 1265 በሚሆኑ ኩባንያዎች መካከል እንደሆነ ይገልጻል፡፡

የአድቮከሲ ሥራዎችን በተመለከተ የግሉ ዘርፍ ከፖሊሲ እና መመሪያዎች ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ከመሰረቱ ለመቅረፍ እንዲቻል የተለያዩ ሰነዶች መዘጋጀታቸውንና በመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የምክክር መድረክ ላይ ቀርበው ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ በተሰጡ ግብዓቶች መሠረት የጥናት ሥራው ሙሉ በሙሉ መጠናቀቁም በሪፖርቱ ላይ ተገልጿል፡፡

የአቅም ግንባታ ሥራዎችን አስመልክቶ የተለያዩ የአቅም ማጎልበቻ ድጋፎች፣ ምክክሮች እና ሥልጠናዎች፣ ለአባል ምክር ቤቶችና የሥልጠና ፍላጎት ለገለጹ ድርጅቶች መሰጠቱንና በተለያዩ መድረኮች በመገኘት የግሉን ዘርፍ የመወከልና የገፅታ ግንባታ ሥራ መከናወኑን ሪፖርቱ ያትታል፡፡

በዕለቱ የበጀት ዓመቱ ኦዲት ሪፖርትም ሪፖርቱን ባዘጋጀው የውጭ ኦዲተር ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት የሂሳብ መግለጫው በበጀት ዓመቱ የነበረውን ሀብትና ዕዳ እንዲሁም ምክር ቤቱ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ያገኘውን የተጣራ ገቢና ወጪ ይገልፃል፡፡

በተያያዘ ዜና የምክር ቤቱ የመተዳደሪያ ደንቡ በ11 ያህል አንቀጾች ላይ እንዲሁም የምርጫ አፈጻጸሙን የሚመለከቱ ነጥቦች ላይ የተደረጉት ማሻሻያዎች ለምልዓተ ጉባዔው ቀርቦ ለውይይት ክፍት ሆኗል፡፡

በአንዳንድ አካባቢዎች በሚፈጠሩ አለመረጋጋቶች በግሉ ዘርፍ ላይ የሚደርሱ መፈናቀሎችን እና የንብረት ውድመት አስመልክቶ ምክር ቤቱ ከመንግሥት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት አሰራር እንዲፈጠር ሲሉም ተሳታፊዎች አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

በቀረቡት ሪፖርቶችና በተሻሻሉት አንቀጾች ላይ የጉባዔው ተሳታፊዎች ሰፊ ክርክር ያደረጉ ሲሆን ተጨማሪ አስተያየቶችንም በመስጠት በአብላጫ ድምፅ እንዲፀድቁ ተደርጓል፡፡

በዕለቱ የኢፌዲሪ ፕሬዚደንት ክብርት ወ/ሮ ሣህለወርቅ ዘውዴ በጉባዔው የመክፈቻ ፕሮግራም ላይ ተገኝተው ንግግር አድርገዋል፡፡

# 11ኛው የኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት በድምቀት ተካሄደ



ክብርት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር ወ/ሮ ፈትለወርቅ ገብረእግዚአብሄር በሪባን ቆረጣ ሥነሥርዓቱ ላይ

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ያዘጋጀው 11ኛው የኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ከጥቅምት 22-26 ቀን 2011ዓ.ም. በኤግዚብሽን ማዕከል በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ተካሄደ፡፡

የዕለቱ የክብር እንግዳ ወ/ሮ ፈትለወርቅ ገብረእግዚአብሄር የፌዴራል ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር በመክፈቻ ንግግራቸው እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ያለቁ ምርቶችንና ቴክኖሎጂዎችን የሚያገኙት ባደጉ ሀገሮች ላይ ጥገኛ በመሆን ሲሆን ያደጉ ሀገሮች ግን ጥሬ ዕቃዎችንና ባመዛኙም የግብርና ጥሬ ምርቶችን ከታዳጊ ሀገሮች ያስገባሉ ብለዋል፡፡

ይሁንና የኢትዮጵያ መንግሥት ለግብርና ጥሬ ዕቃዎች እሴት ለመጨመር ለአምራች ኢንዱስትሪው ትኩረት የሰጠ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ በማውጣት እየሠራ መሆኑን በመጥቀስ ለዚህም ይረዳ ዘንድ የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚሰማራበትን ዕድልም እያመቻቸ ነው ሲሉ የኢንዱስትሪ ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚደረገውን ጥረት ገልጸዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ ያለ ንግድ እንቅስቃሴ የአምራች ኢንዱስትሪው ብቻውን የሚያመጣው ትርፍ ስለማይኖር ዘላቂና አስተማማኝ የንግድ እንቅስቃሴ ሲኖር የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍም በዚያው ልክ እያደገ ይሄዳል፡፡ ‹‹በመሆኑም›› ይላሉ ሚኒስትሯ፣ ‹‹በመሆኑም እንደ የንግድ ትርዒት ያሉ ኩነቶች ኢንዱስትሪን ለማሳደግ በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው፡፡››

የምክር ቤቱ ምክትል ፕሬዚደንት አቶ አሰፋ ገብረስላሴ በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግራቸው እንደተናገሩት ‹‹የኢትዮጵያን ይግዙ›› በሚል መሪ ቃል የሚዘጋጀው ኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ዓላማ የሀገር ውስጥ ምርትና አገልግሎትን በማስተዋወቅ የገበያ ተወዳዳሪነትን ማሳደግና ኢንቨስትመንትን መሳብ ነው፡፡

እንደ ምክትል ፕሬዚደንቱ የንግድ ትርዒቱ ምርቶችን ከማስተዋወቅ ባለፈም የሀገር ውስጥ የገበያ አቅምን የማጠናከር ዓላማም አለው፡፡ የዘንድሮው 11ኛው የንግድ ትርዒት ላይ አዳዲስ የሀገር ውስጥ ምርቶች ይተዋወቃሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም አቶ አሰፋ ተናግረዋል፡፡

እስከ ጥቅም 26 ቀን 2011 ዓ.ም. በቆየው የንግድ ትርዒት ላይ ከሱዳን፣ ሶማሊ ላንድ፣ ግብፅ፣ ሞሮኮ፣ ኢራን፣ እንግሊዝ፣ ቻይናና የመሳሰሉት ሀገሮች የተውጣጡ 13 የሚጠጉና 200 ያህል የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ከቤት ዕቃዎች እስከ አልባሳት፣ ከምግብ ውጤቶች እስከ መድኃኒትና የመዋቢያ ምርቶቻቸውን አቅርበዋል፡፡

## የኢፌዲሪ ፕሬዚደንት የመንግሥት ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ቃል ገቡ

የኢፌዲሪ ፕሬዚደንት ክብርት ወ/ሮ ሣህለወርቅ ዘውዴ ጥቅምት 26 ቀን 2011 ዓ.ም. በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል በተካሄደው የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት 9ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በክብር እንግድነት በመገኘት ንግግር አደረጉ፡፡

ክብርት የኢፌዲሪ ፕሬዚደንት በንግግራቸው የግሉን ዘርፍ ልማት በተመለከተ ከመንግሥት ሊሰጥ ስለሚገባው ትኩረትና ድጋፍ እንዲሁም ከባቢያዊና ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ ከግሉ ዘርፍ ስለሚጠበቀው ግዴታም አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

በመሆኑም የግሉ ዘርፍ ንግድና ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ እየተጫወተ ያለውን ሚና በማስታወስ መንግሥት የግሉን ዘርፍ አላሠራ ያሉትን ፖሊሲዎች ከማሻሻል ጀምሮ




*ክብርት የኢፌዲሪ ፕሬዚደንት ጉባዔውን በንግግር ሲከፍቱ*

ያሉትን የፋይናንስ፣ ሎጂስቲክና ቴክኒካል ድጋፎችን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ቃል ገብተዋል፡፡

ምክር ቤቱ ካስቀመጣቸው ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች መካከል የንግዱ ማኅበረሰብ ስነምግባርን በጠበቀ መልኩ እንዲሰራ እና ማህበራዊ ኃላፊነትን እንዲወጣ ዕውቀቱን እና ግንዛቤውን በማሳደግ ተወዳዳሪ እንዲሆን ማስቻል እንደመሆኑ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ከመወጣት አንፃር የበኩሉን አስተዋፅዖ ማበርከት እንደሚኖርበትም አሳስበዋል፡፡

የግሉ ዘርፍ የአስተዳደር ብልሹነትንና ሌብነትን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል ውስጥ ንቁ ተሳታፊ በመሆን በአጠቃላይ ዘላቂ ልማት ለማስመዝገብ ከመንግሥት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ ታሪካዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣም ሲሉ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

## በሴቷ ቢዝነስ ስኬታማነት ላይ መረባረብ የግሉን ዘርፍ በጠንካራ መሰረት ላይ እንደመመስረት ነው ተባለ





*የም/ቤቱ ዋና ፀሐፊ ለተሳታፊዎች ንግግር ሲያደርጉ*

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ የማህበራት ምክር ቤት ጥቅምት 28/2011 ዓ.ም. በግዮን ሆቴል ለነጋዴ ሴቶች እና ለአነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች የገንዘብ አቅርቦትን አስመልክቶ ባሉ እድሎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ አውደጥናት አዘጋጀ፡፡

የግንዛቤ ማስጨበጫው አላማ ለነጋዴ ሴቶች እና ለአነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች በመንግስትና በግል ተቋማት ያሉ የገንዘብ አቅርቦት ዕድሎቸ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀኃፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ እንደተናገሩት የሴቶች ቢዝነስ ትርፍ መሰብሰቢያ ብቻ ሳሆን 90% የሚሆነውን የቢዝነስ ትርፋቸውን ለሚመሩት ቤተሰብና ለሚኖሩበት ማህበረሰብ ትምህርትና ጤና ላይ መልሰው ኢንቨስት የሚያደርጉት እንደሆነ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ዋና ፀኃፊው ጨምረው እንደገለፁት የጤናማ ኢኮኖሚና ውጤታማ ቢዝነስ መሰረት የሆነውን ቤተሰብና ማህበረሰብ ለማስጠበቅና ለማጠናከር ኢንቨስት ለሚደረገው የሴቷ ቢዝነስ ስኬታማነት ላይ መረባረብ የግሉን ዘርፍ በጠንካራ መሰረት ላይ እንደመመስረት ይቆጠራል፡፡

ለነጋዴ ሴቶች እና ለአነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች የተዘጋጁ የገንዘብ አቅርቦት ዕድሎችን አስመልክቶ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በእናት ባንክ፣ በውሜን ኢንተርፐርነርሸፕ ልማት ፕሮገራም እና በፌደራል የስራ ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተወካዮች የፓወር ፖይንት ገለፃ ተደርጓል፡፡

የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕይራዞች እና ሴት ነጋዴዎች በቢዝነስ እንቅስቃሴያቸው ተገቢውን እድገት ማስመዝገብ እንዲችሉ የገንዘብ ፍላጎታቸውን ከማሟላት ባሻገር በቂና ምቹ የመስሪያ ቦታ፣ የገበያ ተደራሽነት፣ የሚፈለገውን ያህል የትምህርትና የስልጠና እድልም በተሻለ ሁኔታ ማግኘት እንደሚያስፈልጋቸው በውይይቱ ላይ ተወስቷል፡፡

የእለቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ አውደጥናት የፋይናንስ አቅርቦት እድሎችን ጨምሮ በርካታ ጠቃሚ መረጃዎች የተገኙበት እና ሃሳቦች የተንሸራሸሩበት እንዲሁም የፖሊሲ ሪፎርም ለሚያስፈልጋቸው የግሉ ዘርፍ ችግሮች ግብአት የተወሰደበት ሲሆን ከአነስተኛና መካከለኛ ድርጅቶች እንዲሁም በሴቶች ከሚመሩ ኢንተርፕራይዞች የተውጣጡ 53 ተወካዮች ተሳትፈውበታል፡፡

## የምክር ቤቱ ዋና ፀሀፊ በአሜሪካ የሚያሚ ዓለም አቀፍ ንግድ አስተባባሪን ተቀብለው አነጋገሩ

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ዋና ፀሀፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ በአሜሪካ የሚያሚ ግዛት የኢኮኖሚ ልማትና ዓለም አቀፍ ንግድ አስተባባሪ ከሆኑት ዴዝሞንድ አሉፎሃይ ጋር በተለያዩ የቢዝነስ አጋርነት ጉዳዮች ላይ ጥቅምት 19 ቀን 2011 ዓ.ም. በጽ/ቤታቸው ተወያዩ፡፡



የሚ/ር አሉፎሃይ የዛሬው ጉብኝት 15 ዓባል ኩባንያዎችን የያዘ የሚያሚና የፍሎሪዳ ግዛቶች የንግድ ልዑክ እ.አ.አ. በቀጣይ ዓመት በኢትዮጵያ ሊያደርግ ባቀደው ጉብኝት ላይ ለመወያየት ነው፡፡ እንደ ኃላፊው ገለጻ በቀጣይ ወደ ኢትዮጵያ ሊመጣ ያቀደው የንግድ ልዑክ በኢትዮጵያ ስላለው ምቹ የንግድና የኢንቨስትመንት ሁኔታ ዳሰሳ እንደሚያደርግና ከኢትዮጵያውያን አቻ ኩባንያዎችም ጋር የአቻ ለአቻ ውይይት የማድረግ ፍላጎት እንዳለው ታውቋል፡፡

የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊም በኢትዮጵያ ስላለው ምቹ ሁኔታና በምክር ቤቱ የሥራ ኃላፊነት ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በመጨረሻም ሁለቱ ኃላፊዎች በሁለቱም ሀገሮች የንግዱ ማኅበረሰብ መካከል የንግድና የኢንቨስትመንት አጋርነት መፍጠር በሚቻልበት ሁኔታ ላይም አጭር ውይይት አድርገዋል፡፡

# FDRE President Vows to Continue Support




Her Excellency W/ro Sahilework Zewdie, President, the Federal Democratic Republic of Ethiopia, extended the promise of keeping on rendering government support to the development of the private sector.

The President said this in her opening remark as a Guest of Honor on the 9th General Assembly of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations on 5th of November 2018 at Intercontinental Hotel in Addis.

The President reflected her view of what government's concern should be to the development of the private sector in Ethiopia and the corporate social responsibility expected from the private sector.

Recalling the role the private sector plays in the efforts made for trade and investment promotion, Sahilework extended the guarantee that the government would carry on with its support in policy reforms, technical and logistic issues.

The private sector on its part, said the President, should work to ensure its corporate social responsibility so as to support the efforts made in fighting mal-administration and bribery towards realizing a sustainable national economy.

# ECCSA Conducts its 11th Ethio-Chamber International Trade Fair




The 11th Ethio-Chamber International Trade Fair, organized by the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) was held from 1st -5th November 2018 at Addis Ababa Exhibition Center.

In her opening remark, H.E. Fetlework Gebregziabher, Minister of Trade and Industry, said that developing countries like Ethiopia depend on developed countries for finished products and technology, whereas developed ones depend heavily on developing countries for importing primarily agricultural products.

Since the government of Ethiopia is now working to add value to agricultural inputs through the industrialization policy where manufacturing has been given due concern, the government is providing the opportunity to the private sector, she remarked.

"Promotional activities like a trade fair and similar events" she said, "are important for boosting industry."

According to the Minister, the manufacturing sector would continue growing when there is a continuing and lively trade transaction because manufacturing without trading is only a half-way to achieve a desired target.

The Vice President of ECCSA, Assefa Gebresilassie in his welcoming speech said that the Ethio-Chamber International Trade Fair which is held under the motto: "Buy Ethiopian" is mainly aimed at promoting Ethiopian products (goods), services, and industrial inputs to enhance competitiveness of the local industries and attracting investment.

The 'Buy Ethiopian' motto has targeted not only in promoting Ethiopian products to the global market, it is also essentially linked with strengthening capacity of local markets, Assefa added.

According to the Vice President, the 11th Ethio-Chamber International Trade Fair contributes greatly to scale up the Small and Medium Enterprises (SMEs) to the level of Medium and Large Industries (MLIs) as they might explore technological innovations and experiences of those cultures.

On the Fair showing off for five consecutive days, about 213 local and foreign businesses from the Sudan, Somali-land, Egypt, Morocco, Iran, Britain, China and others were exhibiting diverse products from housing furniture to textile manufactures, from food consumptions to cosmetics and pharmaceuticals.

So far, ECCSA has organized successfully ten international trade fairs annually which have brought significant contribution in promoting the country's goods and services and scaling up competitiveness of local industries.

## "Buy Ethiopian" – Said Defines the "Made in Ethiopia" Products





Endalkachew Sime, Secretary General (S.G.) of Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), said Ethio-Chamber International Trade Fair, a trade fair organized by ECCSA, has the objective of promoting local products and services and, to attract investment.

He said this on the opening ceremony of the 11th Ethio-Chamber International Trade Fair held from 1st -5th November 2018 at Addis Ababa Exhibition Center.

Explaining that the event is organized under the motto: "Buy Ethiopian", the S.G. further elaborated that the semantic behind the motto is rather to promote products made in Ethiopia regardless of who produce them-local or foreign companies.

## Secretary General Receives U.S. Business Delegate



Endalkachew Sime, Secretary General (S.G.), of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), held a discussion on October 29 2018 with Desmond Alufohai, International Trade Coordinator, and Miami: Dade County Economic Development and International Trade at his office.

The purpose of his visit, said Mr. Alufohai, to ECCSA was to discuss on the intention that a business delegation of about 15 companies from Miami and Florida (USA) would pay visit to Ethiopia to explore the doing business opportunity the following year.

The companies have interest to also have b2b session with their counterparts in Ethiopia, he said.

Secretary General provided a short brief about ECCSA's responsibility and the available investment opportunity and doing business potentials in Ethiopia.

Finally, they also discussed on how they work together so as to help the private companies of both countries in terms of partnership, promotion of trade and investment.

## Awareness Creation Workshop Organized





The Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) organized Awareness Creation Workshop on Access to Finance for Women Owned Enterprises and Small and Medium Enterprises (SMEs) on November 7, 2018 at Gihon Hotel, Addis Ababa.

The forum was aimed at creating awareness of women owned enterprises and SMEs to have access on financial resources.

A power point presentation about access on financial resources for women owned enterprises and SMEs by Development Bank of Ethiopia, Commercial Bank of Ethiopia, Enat Bank, Women Entrepreneurs Development Program and Federal Job Creation and Food Security Agency has been presented and discussed.

It was discussed that women owned enterprises and SMEs need not only to have access to financial resources but also conducive working place, land, market , education and training opportunities so as to promote their business and to contribute for the growth of the country's economy.

53 representatives from Women Owned Enterprises and SMEs have participated on the Workshop.